## የወያኔ ፓለቲካ ፣ አረመኔያዊ ድርጊትና የምዕራብ መንግስት ዝምታና ስልት

ካለፈው ሰኞ ጀምሮ በኢህአዴግ አገዛዝ በህዝባችን ላይ የተፈጸመውና የሚካሄደው አረመኔያዊ ድርጊት ከአንድ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚልና ፣ አገርን አስተዳድራለሁ ብሎ ከተነሳ አገዛዝ በፍጹም የሚጠበቅ አይደለም። በእነዚህ ሶስት ቀናት የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የባዕድ ኃይል መስሎ በልጆቻችን ፣ በእህቶቻችን ፣ በወንድሞቻችን ፣ በእናቶቻችንና በአባቶቻችን ላይ የፈጸመው እልቂት በታሪክ ዘንድ በፍጹም ሊረሳ አይችልም። እነዚህ ንጹህ ወገኖቻችን በጠበንጃ ሳይሆን ፣ ዱንጋይ ወረወሩ ብሎ የጥይት ናዳ ማውረድና የንጹሃንን ደም ማፍሰስ ፋሺሽታዊ ከማለት በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው በፍጹም አይችልም። ድርጊቱን ፋሺሽታዊ የሚያስብለው ቀደም ብሎ የተጠና ፣ "በጠበንጃ ያገኘነውን ስልጣን በምርጫ አን ለቅም" በሚል ኋላ የቀረና አረመኔያዊ አስተሳሰብ የተዘጋጀ ፣ የህዝብን ፍላጎት ፣ የዲሞክራሲንና የዕድገት ጥማት ለማፈንና "እኛ ባልነው ብቻ መገዛት አለብህ" በሚል እልክ የተሞላበት ፈሊጥ ህዝባችን እየተተራመሰ እንዲኖር ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በደንብ ተጠንቶ በስራ ላይ የዋለና እንዲውል የሚደረግ እርኩስ ተግባር ነው። በተጨማሪም ፣ ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት ለመፈጸምና ፣ ወደፊትም ሊነሱ የሚችሉ ተቃውሞችን በእንጭጩ ለመቅጨት ልዩና ፋሺሽታዊ በሆነ መንገድ የሰለጠነ የሂትለር ዐይነት አፋኝ ጦር መዘጋጀቱ ነው። አግአዚ የሚባለው ይህ ጨካኝ ጦር የህዝቡን ቋንቋ የማይናገር ፣ ከበፊቱ የቆመን ወይንም መሳሪያ ሳይታጠቅ እየገፋ የመጣን ህዝባዊና ሰላማዊ ተቃውሞ በመሳሪያ መጨፍለቅ ነው። ከዚህም ሌላ ፣ የኢህአዴግን ፖለቲካ የሚያራምዱ ጭፍን ፣ ፖለቲካዊ ባህርይና ዕውቀት የሌላቸው ካድሬዎች በኢንስቲቱሽኖችና በተለያዩ የሙያ ማህበሮች በመሰግሰግ ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዳይዳብር ፣ ህዝቡ ችግሩን በውይይት እንዳይፈታ በማፈንና በማስፈራራት ለዕድገት እንቅፋት የሆነ አገዛዝ በአለፉት አስራ አራት ዐመታት ውስጥ እንደሰፈነ የሚታወቅ ነው። ይህንና ጠቅላለውን የኢኮኖሚ ክንውን በተወሰኑ የመን ግስት ባለስልጣኖች ቁጥጥር ስር አውሎ ሌላው በነፃ እየተንቀሳቀሰ እንዳይዳብርና ለጠቅላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅኦ እንዳያደርግ እንቅፋት በመሆን አገሪቱ የባሰ ደህና ለማኝ እንድትሆን አድርጓል። የኢህአዴግ መንግስት ዕውቅ የሆነ የድህነትና ባህልን ከስካሽ የኢኮኖሚክ ፖሊሲ በመከተል ፣ በአገራችን አንድ ወጥ የሆነ እርስ በርሱ የተሳሰረ ኢኮኖሚ እንዳይገነባ በግልጽ አግዷል። ከዚህ ስንነሳ የዛሬውን አገዛዝ ፋሺሽታዊ የሚያሰኙት ብዙ ነገሮች እንዳሉና ከዚህም አንፃር ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነት እንዲሁም ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚደረገው ትግል ልዩ መልክ መያዝ እንዳለበት ግልጽ መሆን አለበት።

እንደሚታወቀው ፣ የግንቦት ሰባት ምርጫ ከመካሄዱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ በብዛት በመውጣት በአገዛዙ ላይ ያለውን ጥላቻና ከእንግዲህ ወዲያም ለእንደዚህ ዐይነቱ የከፋፍለህና ስር ለስር ሲካሄድ ለሰነበተ አረመኔያዊ አገዛዝ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዳማይገዛ አስታውቋል። አንዱን ጎሳ ከሌላ ጋር እያጋጬና ህዝብን እያተራማመሱ መኖር ይብቃኝ በማለት ለአገዛዙና ለዓለም ማህበረሰብም አስተላልፏል። ከእንግዲህ ወዲያ ሰላምን ፣ ዲሞክራሲንና ዕደገትን ነው የምፈልገው ፣ ታሪክን ሰርቼ ለልጅ ልጆቼ ለማስተላለፍ እሻለሁ በማለት ለእነ አቶ መለሰ ዜናዊው አረመኔያዊው አገዛዝ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም እንደዚህ ዐይነት አስከፊ አገዛዝ ብቅ እንዳይልና ታሪክን እንዳያጎድፍ ድምጹን ከፍ አድርጎ አሰምቷል። አንድ ትውልድ የሚጠጋ የግፍ አገዛዝና ህዝብን ማዋከብ በቃኝ ብሎ ብሶቱን መግለጹ ብቻ ሳይሆን ለስልጣኔ ያለውን ጥማትና ፍላጎትም የቱን ያህል እንደሆነ ለንቃው እስኪሰነጠቅ ድረስ በመጮህ ብርሀንን እንደሚሻ አብስሯል። ለዚህም በግንቦት ሰባቱ ምርጫ ማንም ሳያዘውና ሳያስገድደው አመዛዝኖ ፣ አውጥቶና አውርዶ አገሪቱን ሊያስታዳድሩ ይችላሉ ፣ ብቃት አላቸው ፣ ሰላምንና ዲሞክራሲን ያመጡልኛል ፣ የጎሳን ፖለቲካ አሽቀን ጥረው በመጣል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትንና ብሔራዊ ነፃነትን ያጎናጽፉኛል የሚላቸውን ቅንጅትንና ህብረትን ከ 90% በላይ በሆነ ድምጽ መርጧል። ለመምረጥ ከተመዘገበው 26 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 90% የሚሆነው በመብቱ በመጠቀም ፣ ጨለማን ሳይፈራ ፣ ብርድ ይመታኛል ብሎ ሳያስብ ለታሪክ እጅግ በሚያስደንቅ አኳኋን ታሪክን

ሰርቷል ማለት ይቻላል። ይህንን የህዝብ ምኞትና ውሳኔ የፈራውና ሽንፈቴን አልቀበልም ፣ በከፋፈለህና በማተረማመስ ፖሊሴዬ እቀጥልበታለሁ ብሎ ቆርጦ የተነሳው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ በማግስቱ ህገ-መንግስቱን በመፃረር በጠቅላይ ሚኒስተሩ በአቶ መለሰ ዜናዊ አማካይነት የአስቸኳይ ጌዜ አዋጅ በማወጅ ጸረ-ህዝባዊ ድርጊቱን አስታውቋል።ቀጥሎም የታጠቁ ወታደሮች አዲሰ አበባን እንዲቆጣጠሩ ፣ ፖሊሱ በፌደራል አገዛዙ ቁጥጥር ስር እንዲውልና ተቃዋሚ ኃይሎችም በመንግስቱ የዜና ማሰተላለፊያ መሳሪያዎች መጠቀም እንደማይችሉና ስለምርጫው ሄደት በየጊዜው እንዳያስታውቁ አፍኖ በመያዝ ፍጹም አምባገነን መንግስት አሰፍኗል። በገጠር ውስጥ ህዝቡ እራሱን ሊካለከል አይችልም ፤ ሌላ ሶስተኛ ኃይል ሊያየኝ አይችልም ብሎ በመገመት ህዝቡ የሰጠውን ድምጽ በመስረቅና ሌላ በማሰቀመጥ ፣ ወይም ሰርቆ በመጥፋት ፣ አንዳንድ የተቃዋሚ ኃይሎችን ድምጽ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች በመግደልና በማስፈራራት ቀጥታ ወደ ውንብድና ተግባር ተሰማርቷል። ይህ በዚህ እንዳለ አሁንም የምርጫውን ሂደት ህግ በመጣስ እንደገና ለአምስት ዐመት ለመግዛት የሚያስችል በቂ የፓርላሜንት መቀመጫ አግኝቼያለሁ ብሎ የዓለምን ህዝብ ለማሳሳት የውሸት ወሬ ነዝቷል። ይህንንም አንዳንድ የወጭ ጋዜጦች አስተጋብተዋል። በእርግጥም በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን የእነ አቶ መለሰን ማሸነፍ ሲነገራቸው መደንፈቅና መዝናናት ጀመሩ። አንዳንድ የጀርመን ዲፕሎማቶች ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደልባቸው የሚገቡና የሚወጡ እንዲሁም የፈለጉትን ማድረግ የተፈቀደላቸው ሌሎች የውጭ ዜጎች በዚህ አገርን በማዘበራረቅ ፣ አንዳንዱን በማባለግና የአገራችንን ህዝብ የልመና ዘመን ለማራዘም አጥብቀው የሚታገሉ በሚቀጥሉት ጊዜያት እንደሚገፋበት በእርግጥም የልብ ልብ ተሰምቷቸው ነበር። የተቃዋሚው ኃይል ምንም ትርጉም እንደሌለውና የእነ አቶ መለሰ/በረከት ሰመኦን ክሊክ አማራጭ የሌለው መሆኑን ሊያሳምኑን ሞክረዋል።ይሁንና እንደተመኙትና እንደጠበቁት የተቃዋሚው ኃይልም ሆነ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አሜን ብሎ ሊቀበላቸው በፍጹም አልቻለም። ከእንግዲህ ወዲህ ወያኔ በኢትዮጵያ ምድር ፖለቲካዊ ሚናው አክትሟል። ይህንን ሀቅ የዐለም ማህበረሰብ እንዲገነዘበው ይገባል።

ከምርጫው ወዲህ የተከሰተውን የፖለቲካ ሂደትና በተለይም ባለፉት አምሰት ቀናት በህዝባችን ላይ የተፈጸመውንና አሁንም የሚፈጸመውን አሰቃቂ ድርጊት ለመረዳት የዛሬውን አገዛዝ የፖለቲካ ባህርይ ፣ አመጣጥና የመንግስቱን መኪና ጨብጦ አገሪቱን ሙሉ ለሙሉ እንዴት መቆጣጠር እንዳቻለ በመጠኑም ቢሆን መተንተን እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህም በላይ በአገራችን የፖለቲካ ሂደት ውስጥ አሜሪካንና እንግሊዝ እንዲሁም ሌሎች የምዕራብ አገሮች ምን ዐይነት ሚና እንደተጫወቱና ለምንስ የኢህአዴግን አገዛዝ ሙሉ በሙሉ እንደደገፉ ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ለምናደርገው የብሄራዊ ነፃነት ትግል እጅግ አሰፈላጊ ነው። በዚህ መሰረት የዛሬውን አገዛዝ የፖለቲካ ባህርይና ግንዛቤ ለመረዳት በመጀመሪያ በሶስት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ለማተኮር እፈልጋለሁ። እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች እየተነተኑ ማቅረብ ለወደፊቱም የፖለቲካ ክንዋኔ ግንዛቤያችን ያግዘናል ፤ አገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዕድገትን ለማስፈን ከተፈለገ እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች ሳይረዱ ህብረተሰቡን የሚጠቅሙና የአገሪቱን አንድነት ጠብቆ ወደፊት መጓዝ አይቻልም። እነዚህ ሶስት መሰረታዊ ፅንሰ-ሃሳቦች ፣ 1ኛ) ፖለቲካን እንዴት እንረዳለን ፣ የዛሬውስ አገዛዝ ፖለቲካ አካሂዳለው ሲል ምን ማለቱ ነው? 2ኛ) መንግስት ማለት ምን ማለት ነው? አገዛዝስ በመንግሰት ላይ ምን ሚና ይኖረዋል? 3ኛ) አገር ማለት ምን ማለት ነው? በአገርና በብሄራዊ ነፃነት መሀከል ያሉትን ውስጣዊ ግኑኝነቶች እንዴት ነው የምንረዳው?

ብዙ ጊዜ በአገራችንም ሆነ በሌሎች የአፍሪቃ አገሮች የሚካሄዱትን ፖለቲካ ስንመረምር የምንደርስበት መደምደሚያ ፣ በስልጣን ላይ ያሉት መሪዎች ተምረውም እንኳ ፖለቲካን የሚረዱት የአስተዳደር መሳሪያ ሳይሆን የግል ሀብት ማካበቻ ፣ መጠቀሚያና እራሳቸውን ከህብረተሰባቸው በላይ በመገመት የመጨቆኛ መሳሪያ ማድረግ ነው። በዚህም ምክንያት ህብረተሰብና ፖለቲካ አንድ ላይ የሚገናኙ ሳይሆን ፣ ህዝብ እንሳሳዊ ባህርይ እንዳለው በቀላሉ እንደከብት የሚነዳና መብት የሚባለው ፅንሰ-ሃሳብ ለጥቂት በስልጣን ላይ ላሉ ሰዎች ብቻ ተባርኮ እንደተሰጠ ነው በብዙ የአፍሪቃ መሬዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ።

ወደ አገራችንም ስንመጣ የፖለቲካው ግንዛቤ ማርክሲሲት ነው ወይም ስታሊንስታዊ ባህርይ አለው ተብሎ ቢገመትም ፣ እስከአሁን ድረስ በስልጣን ላይ ያሉት መሪዎቻችን የፖለቲካን ትርጉም የሚረዱት እንደግል መጠቀሚያ መሳሪያ እንጂ ፖለቲካ የፍልስፍና መሰረት ያለውና አንድን ህብረተሰብ ለማስተዳደርና ታሪክን ለመስራት የሚያገልግል ልዩ ጥበብ እንደሆነ ተደርጎ አይደለም። ብዙዎችም ተማሩ ቢባሉ እንኳ በፖለቲካ ፍልስፍናና በህብረተሰብ ሳይንስ ከልጅነታቸው ጀምሮ የሰለጠኑ ባለመሆናቸውና ፖለቲካ የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ በደንብ ጭንቅላታቸው ውስጥ የተቀረጸ ባለመሆኑ ስልጣን በሚይዙበት ጊዜ ፖለቲካን የሚረዱት ህብረተሰቡን መበወዣ ፣ አንዱን ማቅረቢያና ሌላውን ማራቂያ ፣ በዚህም ስልጣንን ማደለዳሊያና ህብረተሰቡን መግዢያ መሳሪያ እንጂ ፣ ጥበባዊ ፣ ታሪክን ለመስራት የሚያገለግል ልዩ ፍልስፍና እንደሆነ በፍጹም ግንዛቤ ውስጥ የለም። ያለፉትን ሁለት አገዛዞችን ትተን- ፍልሚያችን ከዛሬው የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ጋር በመሆኑ- የወያኔን የፖለቲካ የፍልስፍና መሰረትና ተግባረዊነት ባህርይ ጠጋ ብለን እንመልከት።

በአገራችን ውሰጥ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ግብግብ ሲደረግና ትንተና ሲሰጥ ህብረተሰብአዊ ክንውኖችን በቲዎሪ ድጋፍ በመመርኮዝ ሳይሆን ፣ አይ በጥላቻ ላይ በመመርኮዝ ወይም ደግሞ በግምት ከዚህም ከዚያም አንዳንድ ነገሮችን በማጣመር አገዛዙን ለመታገል ይሞከራል እንጂ ፣ አገዛዙ የሚመራበትን ፍልስፍና ወስዶ በጣጥሶ በመተንተን አይደለም። ከፖለቲካ አንስቶ እስከ ፖለቲካ ኢኮኖሚና ሌሎችንም ለህብረተሰብ ግንባታ የሚያስፈልጉ ዕውቀቶችን የቲዎሪና የፍልስፍና መሰረት በመስጠት ሳይሆን በዘልማድ የአተናተን ስልት ስለምንጠቀም ህብረተሰባችንን ልንገነባና ልናስተሳስረው የምንችልበት መሳሪያና ዘዴ ከመጀመሪያውኑ ደበዛው ይጠፋል። ረጋ ያለ የቲዎሪ ትንተና- እንደሚባለው ካለቲዎሪ ተግባር የለም- ለመስጠት ገቱ ስለሌለ ፣ ስልጣን ለሚወጡ ሰዎች አገርን እን ደፈለጉት ለመበወዝና ህዝብን አደናግሮ ወደ ብጥብጥ ለማምራት በቀላሉ መንገድ ያገኛሉ። እነ አቶ መለሰና አቶ በረከት ሰመኦን የሚጠቀሙበትም መሳሪያ ይህ ነው። በዘህ መሰረት የአገዛዙን የፖለቲካ ፍልስፍና- ፍልስፍና ካለው- ከተለያዩ የፖለቲካ ፍልስፍና ቲዎሪዎች ጋር በማገናዘብ የገባበተን የዙሪያ ጥምጥም ለማሳየት እሞክራለሁ።

ወያኔ በአወቃቀሩ ማርክሲስታዊ እንደሆነና ይህንን እንደፖለቲካ መሳሪያ አድርጎ ህብረተሰብን መቆጣጠር እንደቻለ ብዙዎች ጽፈዋል። አንዳንዶችም አልባኒስታዊ ነው የሚሉ አሉ። እንደዚህ የሚባለው ብዙውን ጊዜ የድርጅቱ አወቃቀር ከላይ ወደታችና አንዱ አንዱን እየተቆጣጠረ የአንድ ሰው አምባገነንነት ወይም የማያፈናፍን የፓርቲ ቁጥጥር አለበት ለማለት ታስቦ ይመስለኛል። የፓርቲው ወይም የበላይ አካል የሚባለው ከላይ ወደ ታች የበታች አካሎች የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ ጥያቄ ውስጥ ሳያስገቡ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። ከላይ የመጣን ትዕዛዝ የሚቃወምና ተግባራዊ የማያደርግ እርምጃ ይወሰድበታል። ይህ ዐይነቱ አተናተን ግማሽ ዕውነት ቢሆንም የዛሬውን አገዛዝ ባህርይ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት የሚረዳን አይመስለኝም። ምክንያቱም የዛሬውንም ሆነ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ውስጥ ተነስተው የወደቁት ኃይሎችንና ዛሬም ተንጠባጥበው የቀሩትን ድርጅቶች ታሪክ ስንመረምር የምናገኘው መልስ በመሰረቱ በወዳጅና በጠላት ላይ የተመሰረተ ፣ የአንድን ድርጅት ርዕዮተ-ዓለምና የትግል ስልት ያልተከተለ እንደጠላት የሚቆጠርበት ፣ ፖለቲካ የሚባለው የትግል መሳሪያ በኃይል ላይ የተመሰረተ ፣ በመጀመሪያ በግሪክ ሶፊሰቶች የተፈጠረ ፣ በኋላ ናዚዎች የፖለቲካና የርዕዮተ-ዐለም መሳሪያቸው አድርገው ለዘርኝነት ፖለቲካቸው የተጠቀሙበት ስልት ነው። ይህንን የወዳጅ/ጠላት የፖለተካ ዘይቤ በተለይም የናዚ የህግ ፈላስፋ ካርሎ ሽሚት የሚባለው በፖለቲካ ቲዎሪው ውስጥ በማካተትና በማስፋፋት ፣ ፖለቲካ ጠላትን መውጊያ ፣ ወዳጅን ደግሞ ማፍሪያ ብሎ በመተርጎም የአገዛዙ የፖለቲካ ፍልስፍና አድርጓል። የዚህንም ውጤት ተመልክተናል። ከዚህ ሌላ ፣ ሆበስ የሚባለው የእንግሊዙ የፖለቲካ ፈላስፋ ፓለቲካን በተወሰኑ ሰዎች አካባቢ የሚሽከረከር ፣ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ተቀድሶ የተሰጠና ሰፊው ህዝብ ፖለቲካዊ ባህርይ እን ደሌለውና በዚህም መሰረት በገዢ መደብ በህዝብ ላይ የሚጫን ፖለቲካ ሙሉ ነፃነት

ማስፈን እንደሌለበት ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጣል። ስለሆነም ፖለቲካ የሚባለው ፅንሰ-ሃሳብ ግላዊ ወይንም በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ስር የሚወድቅ እንጂ ህዝባዊ ባህርይ እንደሌለውና ሰፊውም ህዝብ ለመብቱ የመታገል መብት እንደሌለው በተዘዋዋሪ ይጠቁመናል። የሆበስ የፖለቲካ ፍልስፍና በፖሰቲቭ ህግ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ፣ በአንድ ህብረተሰብ ውሰጥ ፣ መንግስት በሌለበት ደረጃ ፣ ህብረተሰቡ በጦርነት ውስጥ የሚገኝና የግዴታም ስርዐትን የሚያሲዝ ከህብረተሰቡ የተነጠለ ፖለቲካዊ አገዛዝ እንደሚያሰፈልግ ይነግረናል። በሆበስ አመለካከት ህዝብ ተፈጥሮአዊ አርቆ የማሰብ ኃይል የለውም ፤ ስለዚህም አንዱ ሌላውን በመፍራትና በጥርጣሬ ውስጥ በመውድቅ ህብረተሰቡ በዘላለማዊ የጭንቅላት ውጥረት ውስጥ የሚገኝ ነው። የማኪያቤሌም የፖለቲካ ፍልስፍና እምብዛም ከዚህ የተለየ አይደለም። የማኪያቤሌ የፖለቲካ ፍልስፍና ግላዊ ስሜትንና ፍላጎትን ለማሟላትና ተቀናቃኙን በማሸነፍ ፣ የራስን ጥቅም ለማሳደድ አንዱን በማቅረብ ሌላውን በማራቅ ስልጣንን ለማጠንከር የሚደረግ የሞት የሽረት ትግል ነው። ስለዚህም ማንኛውም በስልጣን ላይ ያለ ሰው የራሱን የበላይነት ለማጠናከርና ሀብትን ለማካበት ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ አይቆጠብም። በማኪያቤሊ ፍልስፍና መሰረት ፣ የሰው ልጅ አርቆ የማሰብ ኃይል ስለሌለው የሚመራው በስሜትና ግላዊ ጥቅሙን ለማሳደግ ሲል ብቻ ነው። ስለሆነም ሰው በአፈጣጠሩ ህብረተሰብአዊ ባህርይ የሌለውና በመተባበርና በመረዳዳት ፣ አንዱ ሌላውን እያገዘ ኑሮውን ወደፊት የሚገፉ አይደለም። ይህ የሆበስም ሆነ የማኪያቢሊ የፖለቲካ ፍልስፍና የእነ አሪስቶተለስን የፖለቲካ ፍልስፍና ሙሉ በሙሉ ይጻረራል። በፕላቶንም ሆነ በአሪስቶተለስ የፖለቲካ ፍልስፍና መሰረት ፣ ፖለቲካ ከመጀመሪያውኑ ስነ-ምግባራዊና የሞራል ባህርይ ሲኖረው ፣ ወደ ግለሰብአዊ ባህርይና ይዞታ በፍጹም ሊቀየር አይችልም። ይህ በፕላቶን የረቀቀው የፖለቲካ ፍልስፍና አመለካከት እነ ማኪያቢሊና እነ ሆበስ ብቅ ካሉና የራሳቸውን የፖለቲካ ፍልስፍና ካዳበሩ በኋላ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአውሮፓውን የፖለቲካ ፍለስፍና በጭንቅላቱ እን ዲቆም አድርጓል። ይህ የፖለቲካ ፍልስፍና ከወያኔ የአገዛዝ ፍለስፍና ጋር እንዴት ይያዛል ?

ወያኔ ማርክሲስት ተባለ አልባኒስት በመሰረቱ የፖለቲካ ቲዎሪና ፍልስፍናው ከህብረተሰብአችን የአወቃቀር ሁኔታ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ሲሆን ፣ በተወሰነ የፖለቲካ ክስተት ውስጥ እነ አቶ መለስ የማርክሲዝምን  ቲዎሪ እንደሽፋን አድርገው ግን ደግሞ ዋና አላማቸው ስልጣንን በመሳሪያ ኃይል ጨብጦ አገርን ለመከፋፈልና የአገሪቱን ሀብት ለመቆጣጠርው ከነበራቸው የረጅም ጊዜ ህልም የመነጨ ነው። በውስጥ የነበረው የተለያየ አመለካከት ከተደመሰሰና መሳሪያን ፣ ተንኮልንና ሸወዳን እንደዋናው የፖለቲካ ፍልስፍናው የወሰደው የእነ አቶ መለስ/ በረከት ክንፍ የበላይነትን ከተቀዳጀ በኋላ ሂደቱ ሁሉ እሱን ከሚመስሉት ፣ ስልጣን ላይ መውጣት የሚያግዙትን ኃይሎች ፣ ሰይጣንም ቢሆን ከነሱ ጋር መወዳጀትና በኢትዮጵያ ምድር ላይ በጎሳ ላይ የተመሰረተ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ማስፈን ነው። ለዚህም በመጀመሪያ አቶ መለሰ ከጦር ሜዳ ሲሰወርና በኋላም በአሸናፊነት ወጥቶ በዓለም አቀፍ የሲናርኪሰት መዳፍ ውስጥ ሲወድቅ ይህንን የፖለቲካ ግቡን ተግባራዊ ለማድረግ እንደነበር ፍንጮች ያመለክታሉ። ከሴአዬው ፓውል ሂንዘና በኋላም ከአንዳንድ የምዕራብ ፖለቲከኞች  ጋር  የጠበቀ ግኑኝነት መመስረትና ከምዕራቡ ድጋፍ ማግኘት የእነመለሰ ክንፍ የቱን ያህል በአለም አቀፍ የአገዛዝ ሂራርኪ ውስጥ እንደወደቀና ፣ አሜሪካና እንግሊዝም የኢትዮጵያን ህብረ-ብሄር አገዛዝ ለመደምሰስ ፣ ወይም ደግሞ አገራችን በዘለዐለማዊ ወዝግብ ውስጥ እንድትዘፍቅና ህዝቦቿ በድህነት ዐለም ውስጥ እየዋኙ የዕድገትን ጭላንጭል ሳያዩ እዚያው እየታሹ እንዲኖሩ ከታለመው ዕቅድ ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው። በአውሮፓውያን አቆጣጠር  በ1991 ዓ.ም ለንደን ላይ በአሜሪካን እምባ ጠባቂነት ፣ ህውአት ፣ ኢፒኤልኤፍና የኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅት ሲሰበሰቡና አገሪቱን ለመቆጣጠር ሲስማሙ ፣ በአንድ በኩል የእነመለስ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ህብረ-ብሄርን የማደከምን ፣ ትናንሽ እራሳቸውን የማይችሉ ግዛቶችን በመመስረት ጠቅላላው ህብረተሰብ ወደ ውስጥ የጠነከረና እርስ በርሱ የተያያዘ  ኢኮኖሚ ገንብቶ ሙሉ ነፃነቱን እንዳያሰጠብቅና ብሄራዊ-ነፃነትን እንዳይቀዳጅ የታቀደ ትልቁ ዕቅድ(Grand design) ነው ማለት ይቻላል። እነ አሜሪካም ለዚህ ትልማቸው ለነ መለሰ ያቀረቡላቸው ግለሰቦች እንደነ ክፍሌ ወዳጆ የመሳሰሉ የሲአይኤ ሰዎችና የራሳቸውን የፊውዳል ድርጅት ያፈራረሱና

ሌሎችንም ድሮ በማርክሲስትነት የሚታሙና ኋላ አቋማቸውን በመቀየር የስልጣን ተከፋይ እንሆናለን ብለው የሚጠባበቁ ምንም ዐይነት ፕርንሲፕልና የፖለቲካ ፍልስፍና የሌላቸውን አድር ባየች በመጠቀም ነው። እዚህ ላይ እነመለስ የፕርንሲፕል ሰዎች አለመሆናቸውንና ለስልጣንና ለከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ከሚያመቻቸው ሰይጣኖች ጋር ሁሉ የተቀደሰ ጋብቻ እንደሚያደርጉ ነው። በወቅቱ ጊዜ መጣልኝ ብሎ ለስልጣን ያላሰፈሰፈ ኃይል ጥቂት አልነበረም። ማርክሲስት ሆነ አልሆነ ፣የጎሳን ፖለቲካ ናፈቀ አልናፈቀ አድርባይ የእነ አቶ መለስን የከፋፍለህ ግዛና አገርን የማዳከም ባህርይ ያለው መንፈሰ ደካማ ሁሉ ትንሽም ቢሆን ስልጣን የማግኘት ዕድል ነበረው።ይህ ዐይነቱ ትዕይንት በደርግ አገዛዝ ዘመንም የታየ እንደ ነበር የታወቀ ነው።

ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ አምባገነንትን ለማሰፈን እንደሚያመች ፣ በአንድ በኩል የክልልን ፖለቲካ ተግባራዊ ሲያደርግ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ካድሬዎችን በመሰግሰግና የሚቃወሙትን ወይ መመንጠር ካሊያም በጭንቀት ዓለም ውስጥ ወድቀው ፍዳቸውን እንዲያዩ በማድረግ ነው። ከደርግ መውደቅ በኋላ ህብረተሰብአዊ ዕርቅ ማድረግ ሲገባና ህዝቡ ተረጋግቶ አገር እንዲገነባ የለሰለሰ ፖለቲካ መከተል ሲገባ ፣ እነ ወያኔ መከተል የጀመሩት ፖለቲካ  አድርባዮችንና  ከየብሄ-ረሰቡ የተውጣጡ ግለሰቦችን  በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በመሰግሰግ መተማመን እንዳይሰፍን በማድረግ ነው። ይሁንና ደግሞ መስሪያ ቤቶችንም ሆነ ህዝባዊ ድርጅቶችን የሚቆጣጠሩት የወያኔ ካድሬዎች እንደሆኑ ማንም የሚያውቀው ነው። በአንድ መቀስ የተከመከሙ ይመስል ፣ ከጠቅላለው የትግሬ ብሄረ-ሰብ ሳይሆን ፣ ከዚያው የትግሬ ብሄረ-ሰብ ውስጥ ከአንድ አካባቢ ብቻ የመጡና ዘረኝነትን ፍልስፍናቸው ያደረጉ የዋህ ግለሰቦችን ተቆጣጣሪዎች በማድረግ ነው። ይህ ሀቅ ስለሆነ ዛሬ ማንም ሊክደው አይችልም። ከዚህ በተረፈ ፣ ወያኔና ኢፒኢኤልኤፍ አዲሰ አበባን በሚቆጣሩበት ወቅት ዱዋል ፓወር እንደተመሰረተና ይህም ለጠባቸው መነሻ መሆኑና ፣ አንተ ኢትዮጵያን አትግዛም እኔ ነኝ የምገዛው በሚል ግብግብ ለጦርነቱ ዋናው መነሻ እንደሆነ ግልጽ ነው። ያም ሆነ ይህ ወያኔና ኢፒኢኤልኤፍ በአፈጣጠረቸውና በፖለቲካ ፍልስፍናቸው ሲጸነሱ ጀምሮ አምባገነናዊ ባህርይ እንደነበራቸውና ይህም ደብቅ ባህርያቸው ለዛሬው የነሱ ፋሺዝም ምንጭ እንደሆነ መታወቅ አለበት። በአዲሰ አበባ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ቢሰፍን ይህ ክስተት ግን የህብረተሰቡ ውቅርና እዚያ ያለው የምሁር ኃይል አላፈናፍን ስላለው እንጂ ኢህአዴግ ዲሞክራት ሆነ ስለወጣ አይደለም።

የእነ አቶ መለሰ ፖለቲካ ጎሳዊ ሽፋን በመስጠትና የብሄረ-ሰብ ነፃነት አራማጅ በመምሰልና ብዙ ወንድሞቻችንን በማታለል የፖለቲካውን አየር እንደመረዙት የማይካድ ሀቅ ነው። ክልል ፖለቲካን ከዕውነተኛ ነፃነት ጋር ያምታቱ ከተለያዩ ብሄረሰ-ቦች የተውጣጡ የዋህ ወንድሞቻችን ከዚህ የፖለቲካ ቁማር ጨወታ በስተጀርባ የሚካሄደውን ትዕይንት ባለመገንዘብ በቀላሉ ወደ ጥላቻና አማራ ነኝ ወይም ደግሞ ለአንድነት እታገላለሁ በሚለው ግለሰብ ላይ እንደተነሱበትና በመጀመሪያ የስልጣን ሽሚያ ዘመን በብዙ ሺህ የሚቆጠር የዚህ የፖለቲካ ተንኮል ሰለባ በመሆን ህይወቱን እንዳጣ ፣ ከመንደሩ እንደተፈናቀለና ህብረተሰብአዊ ቀውስ እንደተከሰተ ይታወቃል።የዚህ መዘዝ በተለይም በአዲስ አበባ ጎልቶ ይታያል። በተለይም ፖለቲካን በዚህ በማከረባበትና በመሸወድ ዐይነት የተረጎሙት ንፁህ ወንድሞቻችን በዛሬው ቀውጢ ወቅት የሚካሄደው የወንድሞቻችንና የእህቶቻችን ደም መፍሰስ አስፈላጊ እንደሆነ አድርገው ያሰቀምጣሉ። ቅንጅት ስልጣን ቢይዝ ትምክህተኝነትን እንደገና እንደሚያሰፍንና ነፃነታቸውን እንደሚገፈፉ የማያስፈልግ ወሬ ያራግባሉ። ይህ አባባል ፊደል ካልቆጠረው ንፁህ ወገናችን ሳይሆን ትንሽ ፊደል ቆጥረናል ከሚሉ ከዚህም ከዚያም ብሄረ-ሰብ የተውጣጡ ግለሰቦች የሚሰነዘር መሰረት የሌለው አሉባልታ ነው። እውንስ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በቁሳቁስ የሚለካ ዕውነተኛ ነፃነት ተጎናጽፏል ? የኑሮው ሁኔታ ተሻሽሎለታል ወይ ? ህክምና እንደልብ ያገኛል ወይ? ንጹህ ውሀስ መጠጣት ይችላል ወይ ? ልጆቹስ የመማርና በኋላም የስራ ዕድል የማግኘት መንገድ ተከፍቶላቸዋል ወይ ? ከተማዎች እየተገነቡና ህዝቡ ከድህነት እየተላቀቀ ነው ? ወይስ በዚህ የክልል ፖለቲካ በስልጣን ላይ ያሉት ብቻ ናቸው ተጠቃሚዎቹ ? ባጭሩ በክልል ፖለቲካው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ምን

ጥቅም አገኘ? እንደዚህ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ውድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሊያነሱና መልስ ሊሰጡ በፍጹም አይችሉም።

ከዚህ አንፃር የእነ አቶ መለሰን ፖለቲካ ስንመረምር በምንም ዐይነት ህብረተሰብአዊ ባህርይ እንደሌለውና አንድን አገር የማያረጋጋ ፣ ፖለቲካን የግል ያደረገ አደገኛና ህዝባችን በዘለዐለም ትርምስ ውስጥ እንዲኖር ሆን ብሎ የታሰበበትና የነሱንና የውጭ ኃይሎችን ጥቅም ለማስጠበቅና የድህነታችንን ዘመን ለማራዘም የተጠነሰሰ ሴራ ነው ማለት ይቻላል። ጠባብነትን ፣ ቂም በቀልነትን ፣ አልበገር ባይነትን ፣ በውይይት ሳይሆን በመሳሪያ ኃይል በመመካት ጠላት ነው በሚለው ኃይል ላይ ስውርና እንደአስፈላጊነቱ ግልጽ ጥቃት መፈጸም ፣ ህዝብን ማዋከብና የተደላደለ የምሁርና የከበርቴ መደብ እንዳይዳብር ያነጣጠረ ፋሺሽታዊ ፖለቲካ ነው። በህብረተሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ቅራኔዎችን በዝግታና በውይይት እን ዲሁም ደግሞ በመግባባት መፍቻ መሳሪያ ከመጠቀም ይልቅ ያሉትን ቅራኔዎች በማባባስ ህዝባዊ ትርምስ መቀጠል አለበት። የነ መለስ/በረከት ሰመኦን ፖለቲካ ፍልስፍና ህዝብን ማወከቢያና መሳደቢያ እንዲሁም ዝቅ አድርጎ የሚመለከቱበት መሳሪያ ሆኗል። በሌላ ወገን ደግሞ እንደዚህ ዐይነት ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ቢታይምና የአገራችንን ፖለቲካ ያመቀው ቢሆንም ፣ ሙሉ በሙሉ ፖለቲካዊ ፍልስፍናው አንድ ወጥ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም። በአንድ በኩል ጥራዝ ነጠቅ የሆነ ማርክሲስታዊ ሽፋን አለው። በሌላ ወገን ደግሞ የጎሳን ፖለቲካ መሰረቱ በማድርግ አገዛዙን እስካሁን አቆይቷል። ከዚህም በላይ ፣ ሳያውቀው ፖለቲካን ግላዊና የአምባገነንነት መሳሪያ በማድረግ ጥቂት ሰዎች በ 70 ሚሊዮን ህዝብ ላይ እንደ ልባቸው እንዲፈነጩ ያደረገ ነው። በተጨማሪም ፖለቲካን የራስን ኬነ መሳሪያና ማሳደጊያ በማድረግ ማኪያቤላዊ ጨወታ የሚጫወትበትና ህብረተሰቡን እን ደፈለገው የሚበውዝበት ነው። ይህ ዐይነቱ ዝብርቅርቁ የወጣ ግን ደግሞ እራስን ማጠናከሪያ የፖለቲካ መሳሪያ ሰሞኑን እንዳየነው ወደ ፋሺዝም በመጠጋት የአገዛዙን ምንነት በግልጽ ያሳየ ነው። አደገኛና በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል ከዚህ ገፋቶ በመሄድ ከፍተኛ እልቂት ለማካሄድ የተዘጋጀ ነው። ትግላችን ውስብስብ ነው ማለት ነው። ይህንን ጉዳይ ለመረዳት መንግስት የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ በመጠኑም እንመልከት።

አሁንም በኛ አገር ያለው ችግር መንግስት የሚለው ፅንሰ-ሃሳብና ተግባሩስ ምን እን ደሆን በግልጽ ተተንትኖ ያልተቀመጠ መሆኑ ነው። ለብዙዎች ፣ በተለይ መሳሪያን ተገን አድርገው ወይም ደግሞ ርዕዮተ-ዓለምን ፍልስፍናቸው ላደረጉ ፣ መንግስት ማለት መፈንጫ መሳሪያ እንጂ ህብረተሰብአዊ ፍላጎት ተግባራዊ የሚሆንበትና ህዝብ አለኝታዬ ነው ብሎ የሚመካበት ልዩ ተቅዋም አይደለም። በተለይም አገዛዝና መንግስት አንድም ሁለትም ሆነው በሚታዩበት አገር መንግስት ማለት ህብረተሰብአዊና ህዝባዊ ባህርይ ያለው ሳይሆን ጥቂት ግለሰቦች ህግና ደንብን ጥሰው ለጭቆና መሳሪያ የሚገለገሉበት ማስፈራሪያ መሳሪያ ነው። በዚህም ምክንያት ፣ በተለይም በጥሩ የፖለቲካ ፍልስፍና ጭንቅላታቸው ያልተገራ ሰዎች ስልጣን በሚጨብጡበት ጊዜ መንግስት መባለጊያ መሳሪያ በመሆን የአገርን አንድነት ከመጠበቅ ይልቅ ህዝብን ማስፈራሪያና መበተኛ ፣ እንዲያም ሲል ለውጭ የስለላ ድርጅቶች ደረቱን ገልጦ በመስጠት ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት ያለበት ፖለቲካና ሰፊውን ህዝብ የሚጠቅምና እሱንም የሚያሳትፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ተግባራዊ እንዳይሆን ወደ እንቅፋትነት የሚለወጥ ነው።

የኢትዮጵያን የመንግስት አወቃቀር ታሪክ ስንመለከት ህዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ ሆነው የሚኖሩ እንጂ ፣ ህዝቡ መንግስት መከታዬ ነው ፣ ፍላጎቴን ያሟላልኛል ብሎ የሚተማመንበት ተገኑ አይደለም። በዚህም መሰረት የተቋቋሙት የቢሮክራሲው ተቋሞች በሙሉ የገዢውን መደብ ጥቅም ማስጠበቂያ እንጂ ህዝቡ ፣ በአንድ በኩል መብቱን የሚያስጠብቅበት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ግዴታውን የሚወጣበትና አገሩን እጅ ለእጅ ተያይዞ ሊገነባ የሚችልበት መሳሪያው አይደለም። ለምሳሌ የጸጥታ ኃይል የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብና ተግባር ስንመለከት ህዝቡን መሰለያ መሳሪያ ነው። ንጉሱ በህዝቡ ዘንድ ይታሙ አይታሙ እንደሆን ፣ ተንኮል ይሸረብባቸው አይሸረብባቸው እንደሆን ለመሰለልና ምናልባትም ህዝባዊ

ሴራን በእንጭጩ ለመቅጨት የተዘጋጀ እንጂ በምንም ህዝቡን የሚያገለግል ኃይል አይደለም። ስለዚህም በአገራችን ምድር መንግስት ራሱ ለምን እንደሚያስፈልግ እንኳ በግልጽ ለውይይት ቀርቦና ህዝባዊ ባህርይ ያለው መንግስት ምን ዐይነት ቅርጽና ይዘት እን ዳለው በቅጡ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ አይተነተንም። በዘልማድ የሚታይ ፣የማይዳሰስና የማይታይ ስሙም መጠራትና መተቸት የሌለበት ተደርጎ ነው የሚወሰደው። ፍልስፍናም የሌለው በመሆኑ በስልጣን ላይ ያሉ ኃይሎች ለነሱ ቡራኬ የተሰጠ ይመስል መዝናኛና ህዝብን አፋኝ መድረክ አድርገው ይወስዱታል። ይህ ዐይነቱ አመለካከት በደርግም ዘመን በመወሰዱ መንግስት ሙሉ በሙሉ ወደ ጨቋኝነትና ወደ ጦርነት መፍጠሪያ መድረክ በመለወጥ ጠቅላላውን ህብረተሰብ ወደ ውዝግብና ጭንቀት ውስጥ እንደጣለው ለማንኛችንም ግልጽ ነው።

የእነ አቶ መለስ/ በረከት ሰምኦን የመንግስት ፍልስፍናም ከዚህ የመነጨ ፣ ግን ደግሞ በጎሳና በማኪያቤላዊ የፖለቲካ ፍለስፍና ህዝብን ወደ ማከረባበቻ መድረክ የተለወጠ ልዩ ኢንስቲቱሽን ሆኗል። ይህንን የጎሳ ፖለቲካ ተግባራዊ ለማድረግ ሰዎቹ መለወጥ አለባቸው። ወይም ቁንጮ የመንግስት ቢሮክራሲው በወያኔ/ኢህአዴግ ካድሬ ቁጥጥር ስር መውደቅ አለት። ይህ ብቻ ሲሆን መንግስት የሚባለው ፅንሰ-ሃሳብ ህዝባዊ ባህርዬውን በማጣት ለከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው እንዲያመች ሆኖ መዋቀር አለበት። በዚህም መሰረት ከውስጥ ሌሎች ተቀናቃኝና የሚጠረጠሩ ኃይሎችን በማባረር መንግስትና የገዢው መደብ አንድ ላይ በመጣመር ጠቅላለውን ህብረተሰብአዊ ክንውን ይቆጣጠራሉ። በዚህም አማካይነት ቁልፍ ቁልፍ የኢኮኖሚ አውታሮችን በመቆጣጠርና ግላዊ በማድረግ የህብረተሰቡ የሀብት ክምችት ተገርስሶ ጥቂቶች በስልጣን ላይ ያሉ የራሳቸውን የሀብት ክምችት ይፈጥራሉ። በሌላ ወገን ደግሞ መንግስትን ተገን በማድረግ ፣ የመንግስቱን መኪና የሚቆጣጠሩ ግለሰቦችና ተከታዮቻቸውን ከህብረተቡ ውስጥ ብቅ ብቅ የሚሉ ታታሪ ግለሰቦች እንዳይወዳደሯቸው አይ የአስተዳደር ጭቆና ያደርጉባቸዋል ወይም ደግም ህይወታቸውን እስከ ማጥፋት ይደርሳሉ። ባለፉት አስራ አራት ዐመታት መንግስትን ተገን አድርጎ የተካሂደው ፖለቲካ ህዝባዊ የሀብት ክምችት እንዳይፈጠርና አገሪቱ ቀስ በቀስም ከኋላ ቀር ኢኮኖሚ ተላቃ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ እንዳትገነባ በዕውቅ የተካሄደበት ህብረተሰብአዊ ባህርይ የሌለው መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል። ይህ የገዢው መደብ ከመንግስት መኪና ጋር በጥብቅ መቆላለፍ ፣ ለሱ የሀብት ማከማቻ መጠቀሚያ መሳሪያ ማድረግና  ወደ መጨቆኛ መሳሪያነት መለወጥ በልዩ የፖለቲካ ክስተት ገጸ ባህርዩን በማሰየት ወደ አውሬነት መለወጥ ችሏል። ሰሞኑን እንደምናየው መንግስት ወደ አውሬነት በመለወጥ የተደበቀ ፈሺሽታዊ ባህርዬውን ወደ ውጭ በማውጣት ማንነቴን ተጋፋ የሚላቸውን ቡድኖችንም ሆነ ግለሰቦችን ካለርህራሄ ጨፍልቋቸዋል። ህገ-መንግስትና ህግን ሳይፈራ በማንአለኝበት ህዝባዊ እልቂት አውርዷል።

በዚህ ዐይነት የመንግስት ፍልስፍና መሰረቱ ምንድነው? አጋዛዝ ማለትስ ምን ማለት ነው? መንግስትስ ማለት ምን ማለት ነው ? ተግባሩስ ምንድነው የሚለውን ለመመለስና ሰዎችን ለማስረዳት አጅግ አሰቸጋሪ ነው። ምክንያቱም በብዘዎቻችን ዘንድ መንግስት የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ ልዩ ዐይነት ነገር እንደሆነና የማይነካ ፣ መብትህን ለመጠበቅ እስከመጋፈጥ ድረስ መሄድና እሱን ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ በሆነ መርሆ ላይ መገንባት እን ዳለበት በቂ ግንዛቤ የለም።  የመንግሰቱንም መኪና የሚያሽከረክሩትን ሰዎች እንደ ልዩ ፍጡሮች አድርገን ስለምንመለከት የሚደርስብንን በደልና ከወጭም ሆነ ከውስጥ የሚመጣብንን ህብረተሰብን አፍራሽ ድርጊት ዝምብለን እንመለከታለን። በተለይም በመን ግስት ላይ የሚኖረን ፍልስፍና እስካልተለወጠ ድረስ አገርን የመጠበቅ ፣ ህብረተሰብን የማስተዳደርና ካለንበት ዝቅተኛ የዕደገት ደረጃ ወደ ተሻለ ለመሸጋገር ያለን ዕድል በጣም ደካማ ይሆናል ማለት ነው። መንግስት ማለት የህዝብ ክምችት ያለበት ሳይሆን ህብረተሰባዊ ፍላጎትና ምኞት የሚንፀባረቅባት ህብረተሰብአዊ አለኝታ ነው። የእያንዳንዱን ግለሰብ መብት ማሰጠበቂያ መሳሪ እንጂ ማንም እንደፈለገ የሚፈነጭበትና ህዝብን የሚያተረማምስበት መሳሪያ አይደለም። እንደ ላይብኒዝ አስተሳሰብ የመንግሰት ፍልስፍና በአርቆ አስተዋይነት

ላይ በተገነባ የህግ መሰረትና ግለሰብአዊ ፈቃደኝነትን(voluntarism) ባስቀደመ መሰረተ ሃሳብ ላይ መመስረት አለበት። ላይብኒዝ እንደሚለው አርቆ አስተዋይነትና የማሰብ ኃይል በሌሉበት ሁኔታ ህግም ተግባራዊነቱን ያቆማል ወይም ደግሞ መንግስትን የሚቆጣጠሩ የገዢ መደቦች ህግንና ደንብን በመጣስ የፈለጉትን ያደርጋሉ። በሌላ አነጋገር ቲዎሪና ተግባር አንድ ላይ መጓዝ ሲኖርባቸው ፣ ለዚህ ደግሞ ትክክለኛ የመንግስት ፍልስፍና አስተሳሰብ በጭን ቅላት ውስጥ መቀረጽ አለበት። ይህ ግልጽ ሲሆን ብቻ ለዲሞክራሲና ለሀገር ዕድገት የሚደረገው ትግል የሰመረ ይሆናል።

የአንድ አገር መንግስት ምንነትና ተግባር በህገ-መንግስት ውስጥ ቁልጭ ብሎ መስፈር አለበት። ህብረተሰብአዊ ባህርይ እንዳለውና መንግስት ጨቋኝ ሳይሆን የህዝብን ፍላጎት ተግባራዊ መሳሪያ ማድረጊያ እንደሆነ ማንኛወም እንዲረዳው በግልጽ መቀመጥ አለበት። በዚህም መሰረት የመንግስቱን መሳሪያ የሚቆጣጠሩ ሰዎች ተግባራቸውና ኃላፊነታቸው የህዝብን ፍላጎትና ዐላማ ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉ መሆን አለባቸው። አስተሳሰበቻው ቀና መንፈስ ያለውና ለህግ ተገዢ የሆኑ መሆን አለባቸው።የራሳቸውን ፍላጎት ለሟሟላት የሚሯሯጡና በቀላሉ ለውጭ የስለላ መሳሪያ በመሆን የመንግስትን መሳሪያና ተግባር የሚያኮላሹ መሆን የለባቸውም።

ይህንን መንፈስ የሚጻረረው የኢህአዴግ አገዛዝ የመንግሰቱን መሳረያ ሙሉ በሙሉ የግሉ ሀብት በማድረግ የመጨቆኛ መሳሪያ ከማድረግ አልፎ የመንግስቱ መኪና በሙስና እን ዲጥለቀለቅና ኃላፊነቱን እንዳይወጣ ተደርጓል። ህዝባዊ መመከቻነቱ ሙሉ በሙሉ ተገፍፎ ወደ ማስፈራሪያነት በመለወጥ ለአገሪቱ ዕድገት ማነቆ ሆኗል። ይህ አንድ ባህርይው ሲሆን ፣ የሚያስገርመው ነገር ይህም ሆኖ ህገ-መንግስቱ ከሚፈቅደውና ማንም ሰው ከሚገነዘበው ውጭ አገዛዙ ሌላ ህዝብን የመጨቆኛ ግላዊ ባህርይ ያለው ከ 10 ሺህ በላይ የሚሆን አግአዚ የሚባል ሰሞኑን በህዝባችን ላይ ያየነውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ያካሄደ የወያኔ ጦር ሰራዊት አለ። እንደዚህ ዐይነቱ ጦር በተለይም ግራ ኃይሎችን ለመምታትና የኮሙኒዝምን መስፋፋት ለመግታት በሚል ሽፋን ስር በ60 ዎችና በ70 ዎቹ ዓ.ም በመሬት ከበርቴዎችና በሲአይኤ አቀነባባሪት በላቲንና በሴንትራል አሜሪካ የተመሰረተውንና ለብዙ ሺህ ህዝብ እልቂት ተጠያቂ የሆነውን የግል አፋኝ ቡድን የሚመስል ነው። በአገራችንም ምናልባትም በኤርትራ በኩል አድርገው የመጡ ተቀጣሪ የወጭ ወታደሮች ልዩውን የወያኔ ጦር ሳያዘጋጁ እንዳልቀረ አንዳንድ ፍንጮች ያመለክታሉ። ያም ሆነ ይህ የወያኔ የመንግስት ግንዛቤ አደገኛ ብቻ ሳይሆን ያሁኑ የፖለቲካ ሁኔታ ቢለወጥምና ሌላ ኃይል ስልጣን ቢይዝ ይህንን የመሳሰለውን የመጨቆኛ ኃይል ትጥቁን ለማስፈታት አስቸጋሪ ይሆናል። ለሌላ የእርስ በርስ መጨራረስ መሳሪያ ሊያገለግል ይችላል። የኢትዮጵያን አንድነት የሚቀናቀኑ የውጭ ኃይሎችም እንደመሳሪያ ሊጠቀሙበትና አገራችን ልትወጣ የማትችለው ማጥ ውስጥ እን ድትወድቅ ትሆናለች።

ከዚህ ዐይነቱ ኃላፊነት የጎደለው አመለካከትና የመንግስት አወቃቀር ለመላቀቅና አገራችን ውስጥ ዘለዐለማዊ ሰለምና ተከታታይነት ያለው ዕድገት እንዲመጣ ከተፈለገ ፣የአዲሱ የመን ግስት ፍልስፍና እኩልነትንና ሙሉ ነፃነት ለማስፈን በሚለው መርሆች ላይ መመርኮዝ አለበት። ወደ ፊት ስልጣንን የሚረከበው አዳዲስ ትውልድ ጭንቅላቱ በፍልስፍና ፣ በሜታፊዝክስና በፖለቲካል ሳይንስ መታነፅ አለበት። አዲስ ህብረተሰብአዊ ኃላፊነትን ሊሸከም የሚችል ኃይል መኮትኮት አለበት። ህዝብና መንግስት አንድም ሁለትም እንደሆኑ በማያሻማ ሁኔታ መቀመጥ አለበት። ለሰላዮችና ለአገር አፍራሾች የማያመች የመንግስት መኪና መዋቀር አለበት።

ወደ ሶስተኛው ነጥብ ደግሞ ልምጣ። አገርና ብሄራዊ ነፃነት አንድ ላይ የተያያዙ ፅንሰ-ሃሳቦች ለመሆናቸው ባያጠራጥርም ፣ አገር የሚለው አስተሳሰብ አብዛኛውን ጊዜ በዘልማድ ስለሚወሰድ በብዝዎቻችን ዘንድ የብሄራዊ ስሜት ባህርይ ያህልም ሰርጎ የገባ አይመስልም። ይህን ስል ምን ማለቴ ነው ? ከሰላሳ ዐመት በላይ የፈጀ የጦርነት ታሪካችንን ስንመረምር

አገራችን እዚህ ዐይነቱ ውድቀት ላይ የደረሰችው እዚያ ውስጥ በተፈለፈሉ ጉዶች ነው። በዕውቀት ላይ ከተመሰረተ ሰላማዊና ለዘብ ያለ ትግል ይልቅ ለውጥን የግዴታ በአመፅ ብቻ ማምጣት ይቻላል ብለው ባመኑ በተወናበዱ ኃይሎች አማካይነት ነው። እስከ ዛሬም ድረስ በውጭ  ኃይሎች በቀላሉ ልትጠቃና ልትቦረቦር የቻለቸው እነዚህ የውስጥ ኃይሎች አገር ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን መሰረተ-ሃሳብ ከግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባታቸውና የውጭ ኃይልን ተገን አድርገው ህልማቸውን ዕውን ለማድረግ ካላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ወይም ደግሞ አገርን መከፋፈልና ማውደም የተወሃዳቸው ከሀዴዎች አመጽን ብቻ እንደ ዋና መሳሪያ አድርገው በመቁጠራቸው ነው። ለተራ ስልጣን ሽኩቻና ነፃ እወጣለሁ በሚል አጉል ፈሊጥ ከዚህም ሆነ ከዚያ የውጭ ኃይል ጋር በማበር አገራችንን የጦር አውድማ በማድረግ የዋሁን ህዝባችንን ሰላም እንዳያገኝ ተገደደ። በዚህ አርቆ አለማሰብ ትግልና አገርን ማወድም እንደባህል በተወሰደበት የጥቂት ግለሰቦች ፈሊጥ ስንት ሺህ ምሁርና ህዝብ እንደ አለቀ ወደ ፊት በደንብ ተጠንቶ ይወጣ ይሆናል። ፊልምም ይሰራለት ይሆናል። በሌላ ወገን ደግሞ ይህ በየቦታው ተበታትኖ በራሱ ዐለም ውስጥ የሚኖርና የሚታገል ኃይል ለአንድ ዐላማ ቢነሳና ህግንና ስርዐትን አክብሮ አገሩን ሊገነባ ቢችል ካለው ዕውቀት አንድ ሶስተኛውን እንኳ ተግባራዊ ቢያደርግ ሰላም የሰፈነባት ፣ የበለጸገችና ለሚቀጥለው ትውልድ የምትተላለፍን ኢትዮጵያ መመስረት በተቻለ ነበር። እነዚህ ሁሉ ኃይሎች ቢተባበሩ ኑሮ ማን ም አገራችንን ሊደፍር የሚችል አልነበረም። ይህንን ለመገንዘብ መሰረታዊ ነገሮችን መረዳት ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ አገር ማለት ወሰን ያለው ፣ -በምድርም በባህርም ሊወሰን ይችላል- አንድ ህዝብ ከረጅም ጊዜ ሂደት በኋላ በሰላምም ሆነ በግጭት እየወደቀም እየተነሳም ወደ አንድ ማዕከላዊ አመለካከት በመምጣት በአንድ ሰንድቅ ዐላማ ስር የሚተዳደርበት ምድር ነው። አገር ታሪካዊ ክንውን የሚካሄድበት ሲሆን ፣ ሰንደቅ ዐላማ ደግሞ የአንድ አገር መለያ ፣ እንደ አገሮች አመሰራረት ህዝባዊ መስዋዕትነትን የሚያመለክትና ያለፉት እናቶችና አባቶች የተወሳሰበ መንገድ አልፈው አገርን ለተከታዩ ትውልድ ያስታላለፉበት መግለጫና ተከታዩ ትውልድ ይህን መሰረት በማድረግ እራሱን የሚያሰተዋውቅበትና መመኪያው የሆነ የጀግንነት ምልክት ነው። ዛሬ አንዳንድ ከሀዲዎች እንደሚሉት ሰንደቅ ዐላማ ተራ ጨርቅ አይደለም። በተለይም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዐላማ የመስዋዕትነታችን ምልክት ነው። እናቶቻችንና አባቶቻችን በደማቸው የተሰውላትን አገር ለዘላለም እንደናስታውስ ፣ መስዋዕትነትን ፣ ለምለምነትንና ሰላምን አንድ ላይ በማካተት በዚህ የተቀደሰ መንፈስ እንድንታገል የሚጋበዘን ልዩ መልዕክት ማስተላለፊያ ነው። እንደሚታወቀው  አገር ማለት በተጨማሪ አንድ ህዝብ እንደ ህብረተሰብ በመደራጀት ፣ በልዩ ልዩ ሙያዎች በመሰማራት ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ልዩ ልዩ ባህሎችንና እሴቶች የሚያካሂድበትና የሚያዳብርበት ልዩ መድረክ ነው። በታሪክ አገጣሚ ሆኖ በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች ይኖራሉ። የተለያየ ቋንቋም ሆነ የአኗኗር ስልት ያላቸው ግን ደግሞ ተመሳሳይ የታሪክ መሰረት ያላቸው ብሄረ-ሰቦች በአንድ አገር ውስጥ ይኖራሉ። ብዙ አገሮች በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ በመጓዝ አን ድ ወጥ ስርዐትና አመለካከት ሲመሰርቱ ፣ ሌሎች አገሮች ደግሞ ይህንን ማድረግ በፍጹም አልቻሉም። አለማድረጋቸው ደግሞ ክፉት ያለው ሳይሆን ፣ የታሪክን ሂደት ለማጣመምና ለራሳቸው ፍላጎት የሚታገሉ ጠባቦች አንድ አገር ሁልጊዜ በአንድ ብሄረ-ሰብ የሚተዳደርና የዚያም ብሄረ-ሰብ ባህል ብቻ የበላይነትን እንደያዘና ሌላውን በማሰገደድና ያስገደደውን ብሄረ-ሰብ ባህል በመደምሰስ የበላይነቱን ለማሰፈን እንደሚታገል አደርጎ ሲቀርብ ቆይቷል። ይህ ጉዳይ የቅኝ ግዛት አስተዳደር በሰፈነበትና በሌሎች አገሮች የተከሰተ ቢሆንም ፣ በአገራችን ምድር ሙሉ በሙሉ ዕውቅ በሆነ መንገድ ተካሄዷል ብሎ አፍን ሞልቶ መናጋር አይቻልም። ተካሂዷል ቢባልም እንኳ የነበረውን ሂደት መረዳት የሚቻለው በጊዜው የነበረውን የንቃተ-ህሊና ደረጃ ከግንዛቤ ውስጥ ካስገባንና ታሪክን በቅጡ ከተመራመርን በኋላ ነው። ካለበለዚያ ዝምብሎ በጭፍን የሚደረግ ውንጀላና ጥላቻን ያዘለ ዝልፊያ ጨቋኝ ለሚባለውም ሆነ ለተጨቋኙ ህዝብ በፍጹም አይጠቅምም። ስለዚህ ኢትዮጵያን እንደ አገር ግንዛቤ ውስጥ ካስገባን ፣ ልዩ ልዩ ብሄረ-ሰቦች የሚኖሩባት ፣ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገርባትና እንዲሁም ልዩ ልዩ ባህሎች የሚንፀባረቅባት አገር ነች። ከሰማኒያ በላይ የሚሆኑ ብሄረ-

ሰቦች አገሬ ብለው የሚኖሩባት ግን ደግሞ ወደ ፊት ህልማችውን ሙሉ በሙሉ ዕውን የሚያደርጉባትና ታሪክን የሚሰሩባት አገር ነች።በዚህች ዓለም ላይ የተለያዩ ቀለም ያላቸው ህዝቦች ካለምክንያት ያልተፈጠሩትን ያህል- ዐለም የነጭ ወይም የጥቁር ብቻ ብትሆን ደስ እንደማትል መገንዘብ ይቻላል- እያንዳንዱ አገር ካለምክንያት የብዙ ብሄረ-ሰቦች አገር ሆኖ አልተመሰረተም። እንደዚሁም አገራችን ካለ አንዳች ምክንያት የዚህ የውብ ባህልና የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች አገር ሆና ባልተፈጠረችም ነበር። በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ይህንን ቆንጆ ባህልና የአገራችንን ውብ ፀጋ አንድ ላይ በማጣመር የመረቀ ዕድገት ማምጣት አልተቻለም። በተለያዩ ጊዜያት ብቅ ጥልቅ ያሉት አገዛዞች ፣ አንዴም ታሪክን በቅጡ ባለመገንዘብ ፣ ሌላም ከውጭ በሚመጣ ወረራና ከውስጥ ግብግብ በመወጠር አገርን ወደ መገንባት ዓለማ ላይ ሊሰማሩ አልቻሉም። በተጨማሪም የሚወሰዱት ኢኮኖሚያዊና ህብረተሰብአዊ ክንውኖች ከብዙ አቅጣጫዎች አኳያ ተገናዝበው ተግባራዊ ለመሆን ባለመቻላቸው በአገራችን ውስጥ ዝብርቅርቅና ያልተስተካከለ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ መዛባት ሊከሰት ችሏል። ይህም ጉዳይ የቤሄረ-ሰቦችን ጥያቄና አፈታት ውስብስብና ልዩ ባህርይ በመስጠት የአገዛዝ በደል እን ዲፈጸም አስከትሏል። ይሁንና አንድ ብሄረ-ሰብ ብቻውን በአጠቃላይ ማቴሪያላዊ ጥቅምና መንፈሳዊ ደስታን ሙሉ በሙሉ ተጎናጽፎ በሌሎች ብሄረ-ሰቦች ላይ የበላይነቱን ተቀዳጅቷል ብሎ በፍጹም መናገር አይቻልም። ታሪክን ለማጣመም ከሚፈልጉ በስተቀር ፣ በማንኛውም ወቅት ከአንድ ብሄረ-ሰብ ብቻ የተውጣጣ የገዢ መደብ ቢያንስ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት የበላይነትን አልተቀዳጀም።

እንደሚታወቀው በአገራችን ውስጥ የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች ብቻ ሳይሆኑ የተለያየ ዕምነት ተከታዮችም ይኖራሉ። ኢትዮጵያ የአንድ ብሄረ-ሰብ አገር ሆና ተወስዳ በፍጹም አይታወቅም። በዚህም ዐይነት ተተርጉሞ አይታወቅም። በታሪክ አጋጣሚም ሆነ በአንዳድንድ ምክንያቶች የተነሳ በተሳሳተ የአገዛዝ ስልት ፣ አገዛዙ አንድን ብሄረ-ሰብ የሚወክልና የሱን ጥቅም ብቻ ሲያስከብር እንደቆየ ተደርጎ ሲወሰድና አሁንም እንደ መመሪያና የአገራችን ዋናው ችግር የብሄረ-ሰብ ጥያቄ ነው ተብሎ በአንዳንድ የህብረተሰብን አወቃቀርና የህበረ-ብሄረሰብን አመሰራረት በቅጡ ያልተገነዘቡ ኃይሎች ሲነዛና የዋህ ሰዎችን ጭንቅላት ሲመርዝ ከርሟል። ይህ ከተማሪው እንቅስቃሴ የተወሰደው የተሳሳተ ፍልስፍና አገር የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ በደንብ እንዳንገነዘብና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ አገር እንዳንመሰርት እንቅፋት ሆኗል። ብዙዎቻችንም በጥርጣሬ ዐይን እንተያያለን። ብዙዎችን ለማሳመንና በጋራ ለአንድ ዲሞክራሲያዊና ነፃ አገር ተባብሮ ለመስራት ችግር አለ። እንኳን ከተለያየ ብሄረ-ሰብ ቀርቶ ከአንድ ብሄረ-ሰብም የመጡት በመሀከላቸው መተማመን የለም። እንደሚመስለኝ እያንዳን ዳችን በራሳችን ክልል ውስጥ የምንኖርና የራሳችንን ህልም የምናልም እንጂ አገር ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ከሳይንስም ሆነ ከፍልስፍና አንፃር በጭንቅላታችን ውስጥ ሰርጎ የገባ አይመስልም። የዚህ ችግር ዋናው ምክንያት ምንድነው ?

አገራችን የሰሶት ሺህ ዘመን ታሪክ ቢኖራትም ከህብረ-ብሄር አመሰራረት አንፃር ብዙ የሚጎድሏት ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ በሌትሬችር የሚገለጽ ህብረተሰቡን የሚያቅፍና ህብረተሰቡ በሚገባው ቋንቋ የተጻፈ ስነ-ጽሁፍ አልተስፋፋም። ሁለተኛ ህብረ-ብሄራዊ ባህርይ ያለው ቲያትር አልዳበረም። ታላቁ ሺለር እንደሚለን አንድ ህብረተሰብ ብሄራዊ ስሜት እን ዲኖረውና ህብረ-ብሄርም እንዲጠነክር ከተፈለገ የግዴታ ብሄራዊ ባህርይ ያለው ድራማ ማበብ መቻል አለበት። ግጥም ፣ ቀልዶች ፣ ስዕልና ሌሎች ኪነቶች ለአንድ ህብረ-ብሄር ማደግና መበልጸግ እንዲሁም ደግሞ ብሄራዊ ስሜትን ለማዳበር አጅግ አስፈላጊዎች እንደሆኑ የጀርመን ክላሲኮች ያስተምሩናል። ከዚህም በላይ ህብረተሰቡ አንድን ብሄራዊ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ሲረዳና ራሱን መግለጽ ሲችል ውስጣዊ ኃይሉን ማጠንከሩ ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ከውጭ የሚመጣ ጥቃት በቀላሉ ሊቋቋም ይችላል። በተጨማሪም ህብረተሰቡ በመገናኛ ሲተሳሰር ፣ ቆንጆ ቆንጆ ከተማዎች ሲስፋፉ ፣ በስራና በፈጠራ ሲጠመድ የዚያ አገር አካል መሆኑን የበለጠ እየተገነዘበ ይመጣል። ይህ ሁኔታ በሌለበት አገር ፣ ጥቂት ፊደል ቆጠርን የሚሉ ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎት ለማሟላትና ስልጣን ላይ ለመውጣትና ብሎም ህዝብን ለማሰቃየት የጎሳን ፖለቲካ ሽፋን በማድረግ የህዝብን ስሜት ወደ ማያስፈልግ አዝማሚያ እን

ዲያዘነብል ያደርጋሉ። የኤርትራው ጦርነት ፣ የወያኔ የሽምቅ ውጊያ ፣ የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅት እንቅስቃሴና በኡጋዴን ውስጥ የሚካሄደው ጦርነት ከዚህ ጠባብ ስሜት የመነጨ እንጂ በእውነትም ጭቆናን በመቃወምና በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ነፃነትን ለማምጣት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በስድሳኛውና በሰባኛው ዐመታት በነፃነት ስም የተካሄዱት የነፃነትና ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግሎች በሙሉ ዛሬ ከስረው የቀሩት ድርጅቶቹ በአፈጣጠራቸው በፖለቲካ ፍልስፍና እየተመሩ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የነፃነት መቀዳጃያ መሳሪያ መሆናቸውን ለመገንዘብ ባለመቻላቸው ነው።

የዛሬውም አገዛዝ ችግር ከዚህ አገርን እንደጋራ ካለማየትና ፣ አገርም ታሪክ የሚሰራበትና ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ እንደሚተላለፍ በቅጡ ካለመገንዘብ የመነጨ መራወጥ ነው። ጥሎ የሚሄድ ፣ በልቶ የሚያልፍ እንጂ ኢትዮጵያን እንደአገሩ የሚያይ ፣ ርዕይ ያለው አገዛዝ አይደለም። ያለፉትን የወያኔን/ኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ስን መረምር ቅኝ ገዢዎች እንኳ አገርን በእንደዚህ የማውድም ዐላማ ተሰማርተው አያውቁም። ህብረተሰቡን ከማከረባበት አልፎ ከውጭ ኃይሎች ጋር የማያስፈለግ ውል መግባትና መፈራረም ፣ አገርን ማስገንጠልና አገራችን የባህር በር እንዳይኖራት ማድረግ ፣ በጦርነት አሸንፎ የጠላት ክልል ውስጥ ከገቡ በኋላ ጠላትን ሳያንበረክኩና እንደገና እንዳይወር ማረጋገጫ ሳይዙ ለቆ መውጣትና ጠላት እንደገና እንዲወረን ፋታ መስጠት በየትኛውም ሀገርና በሚሊታሪ ሳይንስ ታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም። እንደዚህ ዐይነቱን ወንጀል በመስራት እነ አቶ መለሰ ምናልባት የመጀመሪያዎች ሳይሆኑ አይቀርም። የአፄውና የደርግ አገዛዝ ብዙ በደሎችን ቢፈጽሙም እንደዚህ ዐይነቱን ዐይን ያወጣ ወንጀል ሰርተው አላለፉም። ከፖለቲካም አንፃር ሲገመገም ፣ የፖለቲካን ሀሁ ለሚያወቅ ሰው የሰባ ሚሊዮንን ህዝብ ዕድል ለሶስት ሚሊዮን ህዝብ አሳልፎ መስጠት ምንም ትርጉም ያለው አይደለም። እዚህ ላይ ለማለት የምፈለገው ቀጥታ ወረራ እናካሂድ ሳይሆን ወራሪው ኃይል አስፈላጊውን አፀፋ ሳያገኝ መቅረቱንና መቶ ሺህ ለጋ ወጣት የተሰዋለትን መስዋዕት አገራችን ተገቢውን መልስ ማግኘት እንዳትችል ተንኮል መሸረቡን ለማመልከት ብቻ ነው።

ከዚህ ዐይነቱ የጭንቅላት ጨለማነት ለመላቀቅ የእያንዳንዱ ብሄረ-ሰብ ምሁር ትልቅ የቤት ስራ መስራት አለበት። ከተራ የስልጣን ሽኩቻ አልፎ ራሱን በመጠየቅ አንድነትንና ልዩነትና በማጣመር በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ የጋራ አገር መታገል ከማንኛውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ነው። የማይሆን ወሬ ማውራትና ጥርጣሬ ውስጥ መግባት ፋይዳ የለውም። ከእን ግዲህ ወዲያ ማንም ኃይል አገሪቱን እንደፈለገው ጨፍልቆ ሊገዛ አይችልም። ትክክለኛው የፖለቲካ ስልትም ይህ አይደለም። ህዝቦች እርስ በራሳቸው እንዲፋጁ ካልፈለግን በስተቀር በማያስፈልግ ጊዜ የምናራግበው ነፋስ የኢህአዴግን እቡይ ዐላማና የውጭ ኃይሎችን የተደበቀ ሴራ ነው የምናስተጋባና ተግባራዊ ለማድረግ የምንታገለው። ቁጭ ብሎ መወያየትና መፍትሄ መፈለግ የምሁሮች የመጀመሪያውና የተቀደሰው የትግል ስልት ነው።

ወደ መጨረሻው ነጥቤ ልምጣ። በግንቦት 7 የተካሄደው ምርጫ ሁላችንንም ያስደሰተውን ያህል የገዢውን መደብ ፍርሀት ውስጥ ከትቶታል። በመሆኑም ህገ-መንግሰቱን በመጣስ የአሰቸኳይ ጌዜ አዋጅ አውጇል። ኢህአዴግም ሆነ ቅንጅትና ህብረት የአልጠበቁት ሁኔታ በአገራችን ዕውን ሆኗል። እጅግ በሚያስደስት አኳኋን ምርጫው ከመካሄዱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ሶስት ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ በመውጣት አገዛዙን እንደሚጠላው አሳይቷል። በሳምንቱ እንደገና ለመምረጥ ከተመዘገበው 26 ሚሊዮን ውስጥ 90% የሚሆነው የመምረጥ መብቱን በመጠበቅ አገዛዙን ሂድልኝ ፤ አልፈልግህም ብሎታል። ይህ ሁሉ ተከናውኖ የውጭ የዜና ማሰራጫዎች በአገራችን ምንም እንዳልተካሄደ ዝም ብለው አልፈዋል። አንዳንዶቹ ልክ ኢህአዴግ እንደአሸነፈ ሊያሳምኑን ሞክረዋል። የሰለጠኑትም የምዕራብ መንግስታት ሁኔታውን አፍነዋል። ለምንድነው ይህ ሁሉ ጭንቀትና አፈና ? በእኔ ግምት ብዙ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል። 1ኛ) ቢያንስ በሚቀጥለው አምስት ዐመት የኃይል አሰላለፍ ለውጥ እንደማይመጣ ስሌት ውስጥ ያስገቡ ይመስላል ፣ 2ኛ) የኢትዮጵያን ህዝብ ንቃተ-ህሊና ዝቅ አድርገው ገምተዋል። ደህና ለማኝ ስለሆነ ሰጥ ብሎ እንደሚገዛና

እነሱም እንደልባቸው እንደሚዋኙ ማንቀላፋት ጀምረዋል። 3ኛ) ህዝቡን የሚያደራጅና የሚመራው አይ ተቃዋሚ ኃይል የለም ወይም ደግሞ በአጭር ጊዜ ወስጥ ተደራጅቶ አመራርን ሊሰጥ አይችልም። ይሁንና ያልጠበቁት ሁኔታ ተፈጠረባቸው። ስለዚህ የግዴታ ኢህአዴግ እንዳሸነፈ ድምጽ ሳያሰሙ ነገሩን አደባብሰው ለማለፍ ሞከሩ። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ቅንጅትና ህብረት ስልጣን ቢረከቡ ፖለቲካው ወዴት እንደሚያመራ ስለማያወቁ ፣ ይህ ኃይል ስልጣን ላይ እንዳይወጣ አረንጓዴ መብራት ማሳየት የለባቸውም። በተጨማሪም በኢህአዴግ ዘመን ያገኙትን እንደፈለጉ አገር ውስጥ ገብቶ መዋኘት የሚያጡ መስሎ ታይቶአቸዋል። በዚህም ምክንያት አገራችን የለማኝነት ዘመኗን እንድታራዝም የማይሸርቡት ሴራ የለም። በአሁኑ ጊዜ ከአራት መቶ በላይ የሚሆኑ የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች እንደፈለጉት አገርን ያተረማምሳሉ። አብዛኛዎቹ ሰላዮች ናቸው። በዚህም ምክንያትና በንቀት የተነሳ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እንዳይለወጥ ይፈልጋሉ። ቢሻው የሩዋንዳው ዐይነት ሁኔታ ፣ ካለበለዚያም የዩጎዝላቢያ ሁኔታ እንዲፈጠርና አገራችን ትርምስ ውስጥ እንድትገባ የማይሸርቡት ተንኮል ይህ ነው አይባልም። አነሰም በዛም የምዕራቦቹ ታክቲክም ሆነ ስትራቴጅ ይህ ነው። ከነሱ ቁጥጥር ውጭ የምትወጣና ሳይንስና ቴክኖሎጂን የምታዳብር ፣ ከተማዎችን ገንብታ ህዝቦቿ በደስታ የሚኖሩባትን ኢትዮጵያ በፍጹም አይሹም። ለጊዜው ስሌታቸው የከሸፈ ይመስላል።

ወደ አሜሪካን እንምጣ። የአሜሪካውም ስትራቴጂ ከዚህ እምብዛም ባይለይም ፣ ለብዙዎቻችን ግልጽ ያልሆነ ወይም ደግሞ በተሳሳተ ፓራዳይም የሚመሩ ግለሰቦች አሜሪካን ለዛሬው የአገራችን ውድቀት ተጠያቂ መሆኑን በፍጹም ሊገነዘቡ አይፈልጉም። የሃምሳ ዐመቱን የአሜሪካንን የውጭ ፖለቲካ ለተመለከተ በሰላምና በዕድገት መርሆች ላይ ተመርኩዞ የሚጓዝ ሳይሆን የሱን ጭራዎች በማፍራትና በማስታጠቅ በአገሮች ውስጥ የተረጋጋና ለዕድገት የቆመ መንግስት እንዳይመሰረት ማድረግ ነው።የተፍጨረጨሩ ኃይሎችን በአገሩ ሰዎች እያስመታ በብዙ የሶስተኛው ዐለም አገሮች የምናየውን ውዝግብና ደህነት እን ዲሰፍን በስውርና በድብቅ የሚሰራ ለመሆኑ ማንም የሚያውቅ ነው።ጭንቅላቱ የተሰውረ ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው በአሜሪካን ምሁሮች ተጠንቶ የቀረበው ጥናት እንደሚያስረዳው ለዐለም ሰላም እጦትና ደህነት አሜሪካን በቅድሚያ የሚጠየቅ ኃይል ነው። ዩጎዝላቪያ ብትን ትኗ የወጣው በአሜሪካንና በአንዳንድ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች አማካይነት ነው። በኢራክ ላይ ከአንዴም ሁለቴም የሚካሄደው ጦርነት የኢራክን ህዝብ ነፃ ለማውጣት ሳይሆን በዚያ አካባቢ የእስራኤልን የበላይነት ለማሰፈንና የሚፎካከራት እንዳይኖር ለማድረግ ነው። ከአስራ አምስት ዐመት ጀምሮ ደግሞ ራሽያን ለማፈራረስ ያልሞከረው ነገር የለም። በጆርጂያና ራሽያን በሚያዋስኑ ሌሎች አገሮች የጦር ሰፈሩን በማስቀመጥ ቀጥተኛ የማዳከም ሴራ እያካሄደ ነው። በዩክሬይንና በጆርጂያ የተካሄዱትን ምርጫዎች በገንዘብ በመደጎም የሱን ፖለቲካ የሚያራምዱ ፖለቲከኞች ስልጣን ሊጨብጡ ችለዋል። ይሁንና ወደ ፊት እን ደምናየው የሁለቱም አገር ህዝብ ሰላምንና ዕውነተኛ ዕድገትን በፍጹም እንደማያገኝ ግልጽ ነው። ስለዚህ በአንዳንድ ኢትዮጵያኖች ዘንድ የአሜሪካንን ፖለቲካ በሚመለከት ያለው ግን ዛቤ እጅግ የተሳሳተና አደገኛ ነው። አሜሪካን ወያኔንና ሻቢያን ደግፎና ረድቶ ስልጣን ላይ እንዲወጡ ያደረገ ነው። ውስጥ ለውስጥ ሲከታተል የነበረውን በደርግ ዘመን ኢትዮጵያ የመሳሪያ ፋብሪካ እንደምትሰራና ማምረትም እንደቻለች በአገራችን ሰዎች ኢንፎርሜሽን በማግኘቱ እሱን መደምሰስ ነበረበት። ወያኔና ሻቢያ ስልጣን ሲይዙ በመጀመሪያ የወሰዱት ርምጃ እሱን ማፍረስ ነው። የወያኔ መሪዎች የመሳሪያ ፋብሪካ አያስፈልግም በሚል ወደ ማንኪያና ሹካ ፋብሪካ እንለውጠዋልን በማለት በአገራችንና በህዝባችን ላይ ማሾፍ ጀመሩ። ከዚህ አንፃር አሜሪካን የውሰጡ ፖለቲካ እሱ በሚስማማው መልክ እስካልተዘጋጀ ድረስ ለውጥ እንዲመጣ አይፈልግም። ቢቻል ተቃዋሚውን ኃይል ለመምታትና ለመበታተን የማያደርገው ጥረት የለም። የሚያደባውም ለዚህ ነው።

በኛ በኩል ተንኮላቸውን ተገንዝበን ሳንዘናጋ በአንድነት ትግላችንን ለአንድ አፍታም ጋብ ማድረግ የለብንም። የዛሬው አገዛዝ ከስልጣን ላይ እስካልተነሳ ድረስ አገራችን ሰላም አታገኝም። እውነተኛ ኢኮኖሚ ዕድገት በፈጹም አትጎናጸፍም። የራሱን ሰራዊት ይዞ ህዝባችንን ከሚጨፈጭፍ ጋር እርቅ ማድረግ በፍጹም አይቻልም። እርቅ ለማድረግ ከፈለገ

ያስታጠቀውን የፋሺሽት ጦሩን ትጥቁን ማስፈታት አለበት። ይህ ብቻ ሲሆን ምናልባት ለእርቅ መደራደር ይቻል ይሆናል። ይህ በሌለበት ሁኔታ ተግባቡ ብለው ምዕራቦች ቢጎተጉቱን ሌላ ወጥመድ ውስጥ ሊያገቡን በማሰብ ብቻ ነው። ስለዚህ ትግላችንን ማቋረጥ የለብንም።

ሰላምና አንድነት ለእናት አገራችን !!
ፍቅር ለህዝባችን!!

ዶ/ር ፈቃዱ በቀለ/ ከበርሊን